1. የወንጀል ክርክር በሌሉበት የሚታይበት ስርዓት (የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 161....)

1.1. ዓ/ህግ ባቀረበው ክስ የተከሳሽ አለመቅረብ

በመርህ ደረጃ ክስ መሠማት ያለበት ተከሳሽ ባለበት ነው። በወንጀል ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰው ፍርድ ቤት ቀርቦ ክሱ ደርሶትና ተረድቶት የመሰማት ሕገ መንግሥታዊ መብት እንዳለው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንሥግሥት አንቀጽ 2 ዐ ደንግጓል። ይህ ማለት ግን የወንጀል ክስ ሁሉ ተከሳሽ ፍርድ ቤት ካልቀረበ ታይቶ አይወሰንም ማለት አይደለም።

በሕግ ተለይተው በተመለከቱ ወንጀሎች ላይ ተከሳሽ በሌለበትም ክሱን መርምሮ መወሰን ይቻላል። በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ አራተኛ መድሐፍ አንቀጽ 2 ልዩ ሥነ ሥርዓት በሚለው በምዕራፍ አንድ ቁጥር 160/2/ ሥር ነገሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሽ ካልቀረበ ወይም ለመቅረቱ በቂ ምክንያት የሚሰጥለት እንደራሴ ካልቀረበ እንዲያዝ ትዕዛዝ ፍ/ቤት እንደሚሰጥ ይደነግጋል። በዚህ ትዕዛዝ መሠረት መፈፀም ካልተቻለ ተከሳሹ በሌለበት ነገሩን ለመስማት ፍ/ቤቱ እንደሚያስብበት የዚሁ ቁ. 160/3/ ያስቀምጣል። ከዚህ መርህ ሁለት ነጥቦችን እናያለን። ተከሳሽ ሲቀር የመጀመሪያው የፍ/ቤቱ ተግባር እንዲያዝ ማዘዝ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሌለበት ጉዳዩን ለማየት ማሰብ ናቸው።

አንድን የወንጀል ክስ ተከሳሽ በሌለበት መስማትና መወሰን የሚቻለው በቁ. 161/2/ መሠረት ከ 12 ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራት የሚያሳስር ወንጀል የሠራ ወይም በቀድሞ ወ/መ/ሕግ ቁ. 354-365 በአዲሱ የወንጀል ሕግ ቁ. 343 እስከ 354 ድረስ ያሉ ወንጀሎች ፈጽሞ ጽኑ እሥራት ወይም ከ 5 ዐዐዐ ብር በላይ በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሲሆን እና እንዲሁም በውጭ ሀገር ጥገኛ ሆኖ ጥገኛ ያደረገው ሀገር አሳልፎ ያልሰጠው እንደሆነ ነው ቁ. (161/3/):: ተከሳሹ በቁ. 160/2/ ካልቀረበ ወይም ለመቅረቱ በቂ ምክንያት ካልተሰጠና ወንጀሉ በቁ. 161/2/ እና /3/ የተመለከተው ከሆነ ክሱ በሌለበት እንዲሰማ ይታዘዛል። በቁ. 162 መሠረት ፍ/ቤት በጋዜጣ ማስታወቂያ ተከሳሽ እንዲጠራ የሚያዘው ነገሩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተሰጠበት ቀን ባይቀርብ በሌለበት ጉዳይ እንዲታይ በታዘዘው መሠረት ቀጥሎ እንደሚታይ ለማስታወቅ ነው። ከጋዜጣ በተሻለ በሌላ መንገድ መጥሪያው ለተከሳሽ ሊደርስ ይችላል ከተባለም አማራጩ ለፍ/ቤት የተተወ ነው።

በዚህ ሁኔታ በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ የተፈረደበት ሰው ፍርዱ ውድቅ እንዲደረግለት ፍርዱን ባወቀ በ 3 ዐ ቀን ውስጥ ለፈረደው ፍ/ቤት ማመልከት ይችላል (ቁ. 164,197,198) ማመልከቻውም ተቀባይነት የሚያገኘው ተከሳሹ ፍ/ቤት ያልቀረበው መጥሪያው ስላልደረሰው ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የቀረ መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው። ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ምንድነው የሚለውን የመወሰን ኃላፊነት

የፍርድ ቤቱ ነው። ማመልከቻው ተቀባይነት አግኝቶ ፍ/ቤቱ በሌለበት የሰጠውን ውሣኔ ውድቅ ካደረገው ጉዳዩ/ ክሱ እንደገና በሌላ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት እንዲታይ ይታዘዛል ቁ. 202።

በሌለበት የተፈረደበት ፍርድ እንዲነሳለት ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ የተደረገበት ተከሳሽ ይግባኝ ማለት የሚችለው በቅጣቱ ላይ ብቻ ነው።

1.2. በግል ክስ ፍርድ ቤት አለመቅረብ።

በግል በሚቀርቡ ክሶች ተከሳሽ ባይቀርብ ከላይ በቁ. 162 እና 163 ሥር እንደተመለከተው በሌለበት ክሱ አይቀጥልም። ይህም በግል የሚቀርቡ ተብለው በወንጀል ሕጉ የተቀመጡት ወንጀሎች ግለሰብን እንጂ ህበረተሰቡን በቀጥታ የማይነኩ ግላዊ ባህሪይ ያላቸው በመሆናቸው ነው።

በግል ክስ ተከሳሽ ባይቀርብ ፍ/ቤት ተከሳሹን እንዲያዝ ያዛል (ቁ. 166) ተከሳሹ ባይገኝ ፍ/ቤቱ ለስንት ጊዜ እንደሚያዝ ሕጉ አይመልስም። ተከሳሹ ባለመገኘቱ ደግሞ መዝገቡ በእንጥልጥል ላልተወሰነ ጊዜ በቀጠሮ ማቆየትም ተገቢ አይሆንም። ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም ተከሳሹ በተገኘ ጊዜ ክሱን ማንቀሳቀስ እንደሚችል ጠቅሶ መዝገቡን መዝጋት ይገባል። ክሱ ሊንቀሳቀስ የሚችለው ግን የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜው ከማለፉ በፊት ሊሆን ይገባል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ራሱ ግል ከሳሹ ባልቀረበ ጊዜ ምን መደረግ አለበት የሚለውን ስንመለከተው ደግሞ ግል ከሳሹ ነገሩ በሚሰማበት ቀን ያለ በቂ ምክንያት የቀረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ክሱን ሰርዞ ተከሳሹን ከክሱ ውጭ እንዲሆን ያደርገዋል (165 (1)) ። በዚህ አግባብ ክሱ የተሰረዘበት ግል ከሳሽ ክሱ በተዘጋ በ 15 ቀን ውስጥ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይለት ለፍርድ ቤቱ ማመልከት ይችላል። በተቀጠረበት ቀን ሊቀርብ ያልቻለው ከአቅሙ በላይ በሆነ በቀ ምክንያት መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ሊፈቀድለት አይገባም (165 (2))። በዚህ 15 ቀን ውስጥ ማመልከቻውን ያላቀረበ እንደሆን ወይም አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ያልተቀበለው እንደሆነ የክሱን መሰረዝ አስመልክቶ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ፍርድ የመጨረሻ ይሆናል (165 (3))።

2. የደንብ መተላለፍ ወንጀል ልዩ ስነ ስርዓት

የደንብ መተላለፍ ወንጀል ክርክር ስርዓት ከመደበኛው የወንጀል ስነ ስርዓት የተለዩ ነው። በዓ/ህጉ ወይንም በግል ከሳሹ አመልካችነት የደንብ መተላለፍ ወንጀል ፊጽሚል ተብሎ የተከሰሰ ክሱ እና የፍርድ ቤቱ መጥሪያ በፍር ቤቱ ተልኮለት የደረሰው ተከሳሽ የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት ጥፋተኝነቱን የሚያምን ከሆነ ይህንኑ በጽሁፍ በመግለጽ እና በጽሑፉ ላይ በመፈረም መልሱን ለፍርድ ቤቱ በመላክ ነገሩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ፍርድ ቤት አለመቅረብ ይችላል (168)። እንዲህ በሆነ ጊዜ እና ፍርድ ቤቱም የክሱን ፍሬ ነገር ከዓ/ህጉ ወይም ከግል ከሳሹ አረጋግጦ ፍርድ በመስጠት ግልባጩን ለተከሳሹ እንዲደርሰው ያደርጋል (169 (1)። በዚህ ፍርድ ምክንያትም ፍርድ ቤት የገንዘብ መቀጮ የሚወስንበት ከሆነ ተከሳሹ ባልቀረበበት ወዲያውኑ መቀጮውን

ይወስናል (169 (2))፤ ቅጣቱ እስራት ወይም የግዴታ ስራ በሆነ ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ ማስጠንቀቂያ መስጠት ወይም ወቀሳ ማድረግ በፊለገ ጊዜ ተከሳሹ እንዲቀርብ ይደረጋል። በቀረበ ጊዜም የቅጣት ውሳኔው ከማረፉ በፊት የመከላከል መብት ይሰጠዋል (169 (3))

ተከሳሹ ክሱን የማያምን ከሆነ ነገሩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን መቅረብ ይኖርበታል። ተከሳሹ በቀረበ እና ክዶ በተከራከረ ጊዜ ዓ/ህጉ ወይም ግል ከሳሹ እና ተከሳሹ ምስክሮች ካሏቸው አቅርበው እንዲያሰሙ ይደረጋል። ይህንን ስነ ስርዓትም በቃል በማስፈጸም ፍርድ ቤቱ የምስክሮቹን ዋናውን ቃል ብቻ በመመዝገብ እና ለፍርዱ ምክንያት የሆነውን ነገር እና ህግ በመጥቀስ ባጭሩ በመጻፍ ፈርዱን ይሰጣል (171 1-3)።

ተከሳሹ ለበቂ ምክንያት ነገሩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ያለ በቂ ምክንያት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ወዲያዉኑ ፍርድ ሊሰጥ የሚገባው ስለመሆኑም በቁጥር 170 (3) ተጠቅሷል፡ ይህም ተከሳሹ ያለ በቂ ምክንያት ክሱን በማመን በጽሁፍ ገልጾ ባልላከበት ሁኔታ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ የዓ/ህግን ወይም የግል ከሳሹን ምስክሮች መስማት ሳያስፈልገው ወዲያውኑ ፍርድ ሊሰጥ የሚገባው መሆኑን ያሳያል።

3. በወንጀል ነገር ውስጥ ጉበተው የተገኙ ህጻናት የክስ/የፍርድ/የቅጣት አፈጻጸም ስነስርዓት

ህጻናት በወንጀል ነገር ጉበተው ሲገኙ የሚስተናገዱበት ሂደት የተለዬ ነው። ይህንን ሁኔታ ለመመልከት መጀመሪያ ህጻን ማን ነው የሚለውን ነጥብ ማዬቱ ተገቢ ነው።

3.1. ካለ መጠን ያላደረሰ ሰው (ህጻን) ማለት እስከ ስንት ዓመት ድረስ ያለ ሰው ነው?

ህጻን ማለት ኢትዮጵያ በአፀደቀቻቸው የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን /ህመኮ/ አንቀፅ 1፣ የአፍሪካ ህጻናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተር /አህመደቻ/አንቀፅ 2፣ እና በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 215 መሰረት እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው። እነዚህ ህጻናት ሲያድጉ በስነምግባር ካልታነጹ፣ትምህርት እንዲያገኙ ካልተደረገ እና እንክብካቤ ካልተደረገላቸው ወደ ወንጀል ተግባር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ለሁለመና እድገታቸው የአዋቂዎችን ድጋፍና እገዛ ይሻሉ። ይህ ከተነፈጋቸው ለከፍተኛ አደጋ ይጋለጣሉ። ለዚህ ነው ለጥቃት ከሚጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች /vulnerable groups/ ተርታ የሚመደቡት። በአንድ ሃገር ብሎም በዓለም ላይ መልካም ትውልድ እንዲቀጥል ለማድረግ ህጻናት የተለየ እንክብካቤ እንደሚያስፈልግ አያከራክርም። ለዚህ ነዉ የዓለም ሀገራት ለህጻናት መብት የተለዬ ትኩረት

በመስጠት የህጻናት መብት ኮንቬንሽንን ያጸደቁት (ከአሜሪካ ውጭ)። ይህ በአለም ላይ በህጻናት ጉዳይ ላይ ያለውን የአስተሳሰብ አንድነት ማረጋገጫ ነው።

ህጻናት ገና በአካልም ሆነ በአእምሮ ያልበሰሉ በመሆናቸው ወደ ወንጀል ውስጥ ገብተው ከተገኙ መታየት ያለበት በዋነኛነት ለዚህ ችግር የዳረጋቸው ምክንያት ነው። አጥፍተው ሲገኙ አላማው እነሱን መቅጣት ሣይሆን በቀላሉ ሊታረሙ የሚችሉበት የእድሜ ሁኔታ ላይ ስለሚገኙ የወደፊት ህይወታቸው ፈር የሚይዝበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው። የፍትህ አካላት ሚና መሆን ያለበትም እንደ ሐኪም ችግራቸውን ተረድተው መፍትሔ ማፈላለግ ነው። ለዚህም ተግባር ፍ/ቤቶች የህጻናቱን ችግር ለመገንዘብ የስነ ልቦና እና የማህበራዊ ሣይንስ ባለሙያ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል። እነዚህን ባለሙያዎች በህጻናት ጉዳይ የማሳተፉ አሰራር በአዲስ አበባ የፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤቶች እየተተገበረ ያለ ቢሆንም በዚህ ረገድ በክልላችን ብሎም በሀገራችን በሚገኙ ሌሎች ፍርድ ቤቶች ይህ ነው የሚባል ተሞክሮ የለም። ይህንንም በመገንዘብ የክልላችን ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ በሚገኙ ወረዳ ፍርድ ቤቶች በህጻናት ጉዳይ ላይ የሚሳተፉ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሞያዎችን በመቅር አሰራሩን ለማዳበር ጥረት እያደረገ ነው። በዚህ መልኩ ህጻን ማን ነው? ለምንስ የተለዬ ትኩረት ሊሰጣቸው ተገባ የሚሉትን እና ይህስ እንዴት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል? የሚለውን ከተመለከትን በኋላ ለወንጀል ሃላፊነት የህጻናት የእድሜ ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለውን መመልከቱ አስፈላጊ ነው።

3.2. ለወንጀል ዓላማ በወንጀል ተጠያቂ የማይሆን እስከ ስንት ዓመት ድረስ ያለ ህጻን ነው?

በወንጀል ተግባር ተጠያቂ ሊሆን የሚገባው ህጻን ማለት /criminal majority/ እና ለፍትሐብሔር ተግባር ህጻን ማለት / civil majority/ የተለያየ ነው። ለወንጀል ጊዜ የተጠያቂነቱ እድሜ መነሻ እንደ ሃገሩ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል። የወንጀል ተጠያቂነት የእድሜ መነሻ ግን ከፍትሐብሔር ዝቅ ያለ ነው። በአገራችን የህጻናት ዝቅተኛ የወንጀል ተጠያቂነት እድሜ በወ/ህ/አ 52 መሰረት 9 ዓመት ነው፤ ማለትም ዘጠኝ ዓመት ያልሞላቸው ህጻናት በወንጀል ጉዳይ ሃለፊዎች ሆነው አይቆጠሩም፤ እነዚህ ህጻናት በወንጀል ጉዳይ ተሳትፈው ሲገኙ ቤተዘመዶቻቸው፣ አስተማሪዎቻቸው፣ አሳዳሪዎቻቸው ወይም ሌሎች አካላት ተገቢውን ጥንቃቄ ያደርጉላቸዋል። ዘጠኝ ዓመት የሞላቸው እና ከዚያ በላይ የሆኑ ህጻናት በወንጀል ድርጊት ተሳትፈው ከተገኙ ግን የወንጀል ሃላፊነት ያለባቸው።

3.3. የተለዩ ጥበቃ የሚደረግላቸው አካለ መጠን ያላደረሱ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች ከስንት እስከ ስንት ዓመት ድረስ ያለ ሰዎች ናቸው?

አጠቃላይ በሆነ ሁኔታ ዘጠን ዓመት የሞላቸው እና አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸው ህጻናት የወንጀል ተግባር ፈጽመው ሲጉኙ በወንጀል ተጠያቂነት ይከተላቸዋል። ከእነዚህ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች ውስጥ የተለየ ጥበቃ የሚያገኙት እድሜያቸው 9-15 ዓመት የሚሆኑ ህጻናት ናቸው። ለወንጀል ህግ ተግባር የ 15 ኛ ዓመት ልደቱን ያከበረ ህጻን እንደ አዋቂ ነው የሚቆጠረው። በወ/ህ/ሳ 56 መሰረት እድሜያቸው 15-18 ለሆኑት ህጻናት ጥበቃ የሚያደረገው ከጥፋተኝነት ውሣኔ በኋላ በቅጣት ጊዜ ብቻ ነው። የጥበቃው አድማስ ጠባብ ነው። ሁሉም ህጻናት ሊካተቱ ይገባል የሚል ተቃውሞ በህጻናት ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች ይደመጣል። ወጣት አጥፊነትን የፍትህ ስርዓት ሂደት የሚገዙት ድንጋጌዎች በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 171-180 ያሉት ናቸው።

3.3.1. ከዘጠኝ ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሞላቸው ወንጀል አድራጊዎችን በተመለከተ የሚደረግ ልዩ ጥበቃ

I. ክስ የሚቀርብበት ስነ ስርዓት

በዚህ እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ህጻናት በወንጀል ተግባር ጉበተው ሲገኙ የክስ አቀራረቡ የሚመራው በተለዩ ሁኔታ ነው።

- ፖሊስ፣ ዓ/ህግ፣ ወላጁ፣ ሞግዚቱ ወይም በቅርብ የሚገኝ ዘመዱ በቅርብ ወደሚገኘው ወረዳ ፍርድ ቤት ወዲያዉኑ ይዞት ይቀርባል 172 (1)፤ ወላጁ፣ ሞግዚቱ ወይም በቅርብ የሚገኝ ዘመዱ አብረው ባልቀረቡ ጊዜ እንዳሉ ተጠይቆ ካሉ እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ ወዲያዉኑ መጥሪያ ይልካል 173
- ያመጣው ፖሊስ ወይም ዓ/ህግ የወንጀሉን እና የምስክሮችን ዝርዝር /የአቤቱታ ማመልከቻ/ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ይጠይቀዋል፤ ፍርድ ቤቱም በመዝገቡ ይጽፍና ፖሊስ ምርመራውን የሚፈጽምበትን ሁኔታ የሚገልጽ መመሪያ ይሰጠዋል 172 (2)
- ክሱ ከአስር ዓመት በላይ በሚሆን ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ ሲሆን ክሱን ዓ/ህጉ አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ያዛል 172 (3) ፤ ከእነዚህ ዓይነት ክሶች ውጭ ያሉ ጉዳዮችን ክስ የሚያዘጋጀው እና ክርክሩን የሚከታተለው ማን ነው?

- ጉዳዩ ቀጠሮ የሚያስፈልገው ወይም ለበላይ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ ነገሩ በሚሰማበት ቀን ማቅረብ ለሚችሉ ወላጆቹ፣ ለሞግዚቱ፣ ለዘመዱ፣ እነዚህ በሌሉ ጊዜ ህጻናትን ለመንከባከብ ለተቋቋመ ድርጅት ወይም ራስን ለቻለ ጨዋ ሰው ይሰጣል 172 (4).

II. የነገሩ መሰማት

- እነዚህ አካለመጠን ያላደረሱ ወጣቶች በወንጀል ሲከሰሱ እና ወላጆቹ፣ ሞግዚቱ ወይንም ዘመዱ ባልቀረቡ ጊዜ ወይም የተከሰሱት ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት ወይም በሞት በሚያስቀጣ ወንጀል ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ በጠበቃ እንዲታገዙ ያደርጋል (የወ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 174)
- ሊሰማው የማይገባ ነገር በማስረጃነት ሲቀርብ ወይም ትችት የሚሰጥበት በሆነ ጊዜ ከችሎቱ እንዲወጣ ይደረጋል (የወ/ስ/ስ/ህ/ቁ/175)
- ነገሩ የሚሰማው በዝግ ችሎት ይሆናል፤ ነገር ግን ምስክሮች እና ወላጆች/ሞግዚቶች/የበጎ አድራጊ ድርጅቱ አባሎች ይገኛሉ፤ ጉዳዩ የሚታየው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ዓ/ህግ መገኘት አለበት (የወ/ስ/ስ/ህ/ቁ/176)፤ ይህ ማለት ምን ማለት ከዚህ ውጭ በሆነ ጉዳይ ፖሊስም ሆነ ዓ/ህግ በችሎት ሊገኙ አይገባም ማለት ነው ወይ? በዚህ ነጥብ ላይ ሁለት ዓይነት ሃሳቦች ይንጸባረቃሉ፤፤

    - አንደኛው ሀሳብ የክስ መሰማት ሂደት በዝግ ችሎት ይሁን ወይም አይሁን የሚለው ጉዳይ የሚመለከታቸው ከከሳሽ (ከፖሊስ ወይም ከዓቃቤ ህግ)፣ ከተከሳሽ እና ፍርድን ከሚሰጡ ዳኞች ውጭ ያሉ አካላትን እንደሆነ ስለሚገመት ክሱ ሲሰማ ክሱን ያቀረበው ፖሊስ/ዓቃቤ ህግ ከችሎት እንዲወጣ ሊደረግ አይገባም። ድንጋጌው ሊያስተላልፍ የፈለገው ክሱ ከአስር ዓመት በላይ በሚሆን ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ ባልሆነ ጊዜ ክሱ በዓ/ህግ ሊቀርብ የማይችል በመሆኑ (የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 172 (3)) እና እነዚህ ጉዳዮችም በሚታዩበት ጊዜም ዓ/ህጉ ሊገኝ የሚችልበት አጋጣሚ የሌለ በመሆኑ ጉዳዩ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚታይ እና ክሱም በፖሊስ አማካይነት ተዘጋጅቶ የቀረበ በሆነ ጊዜ በተለዩ ሁኔታ ክሱን ካቀረበው ፖሊስ በተጨማሪ ዓ/ህግ እንዲገኝ ለማድረግ እንጅ ዓ/ህግ አዘጋጅቶ ባቀረበው ክስ መሰማት ሂደት ላይ ዓ/ህጉ እንዳይገኝ (ጉዳዩን እንዳይከታተል) ለማድረግ አይደለም፤ ምክንያቱም የማይከታተለውን ክስ ማዘጋጀቱ ትርጉም የሌለው በመሆኑ እና በጉዳዩ ላይ ምስክሮች እና ወላጆች/ሞግዚቶች/የበጎ አድራጊ ድርጅቶች እንዲገኙ

እየተፈቀደ ክሱን ያቀረበው አካል እንዳይገኝ የሚከለከልበት አግባብ የለም የሚል አስተሳሰብ አለ።

- የተለየው ሃሳብ ደግሞ ድንጋጌው ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ በችሎቱ ውስጥ ማን መገኘት እንዳለበት ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያስቀመጠ በመሆኑ (ምስክሮች እና ወላጆች/ሞግዚቶች/የበጎ አድራጊ ድርጅቶች) ዓ/ህግም ሆነ ፖሊስ ክሱን አዘጋጅቶ ካቀረበ በኋላ በችሎት ተገኝተው ክርክሩን የሚሰሙበት አግባብ አይኖርም የሚል ነው። ይህንም በሚሳይ መልኩ አዲስ አበባ በፊዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አሁን ባለው አሰራር በህግ በታዘዘ ጊዜ ዐ/ህግ ክስ አዘጋጅቶ ቢያቀርብም ክሱን በችሎት ተገኝቶ መከታተል አይፈቀድለትም።
- ከሁለቱ ሀሳቦች አሳማኝ የሚመስለው እና ሊፈጸም የሚገባው የመጀመሪያው ሃሳብ ነው።

- ችሎቱ በሌላ ጉዳይ ተሰይሞ ከሚያነጋግርበት አኳኋን በተለዬ ሁኔታ ተሰይሞ ጉዳዩን መስማት አለበት 176 (2)
- ክሱ በችሎቱ ተነቦለት በሙሉ እንዲያውቀው እና እንዲረዳው ተደረጎ መልስ እንዲሰጥ ከተደረገ በኋላ የቀረበበትን ክስ ያመነ መሆኑ ለፍርድ ቤቱ ግልጽ በሆነለት ጊዜ ይህንኑ በመመዝገብ ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት ይችላል፤ ያላመነ እንደሆነ ግን ለክሱ የተጠሩትን ምስክሮች ፍርድ ቤቱ ይጠይቃል (ይህ ማለት ዓ/ህግ ወይም ፖሊስ ምስክሮቻቸውን መጠየቅ አይችሉም ማለት ነው?) የተከሳሹ ወገንም መስቀለኛ ጥያቄ ሊጠይቁ ይችላሉ። በዚህ መልኩ የቀረቡት ምስክሮች የወንጀል ድርጊቱ መፈጸሙን ካረጋገጡ አካለ መጠን ያላደረሰው ወጣት /እንደራሴው/ጠበቃው ማንኛውም ምስክር እንዲጠራላቸው ማድረግ ይችላሉ፤ ፍርድ ቤቱ ምስክሮቹን በመጠየቅ ክርክሩን ካጠናቀቀ እና የተከሳሹ ወገን ጠቅላላ ንግግር ካደረጉ በኋላ ክርክሩን መርምሮ ፍርድ ይሰጣል 176 (3 - 7)፤ (ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሱት ነጥቦች በተከሳሹ በኩል የሚቀርቡትን መከላከያ ምስክሮችን የተከሳሹ ወገኖች ጥያቄ ሊያቀረ ርቡላቸው አይችሉም ወይ? የሚለው እና ዓ/ህግ ወይም ፖሊስ መስቀለኛ ጥያቄ ሊጠይቀዋቸው አይገባም ማለት ነው? የሚለው ነው።

III. ፍርድ አሰጣጥ

- ወጣቱ ጥፋተኛ ሆኖ ካልተገኘ ወዲያዉኑ በለዓ ይለቀቃል፤ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ግን በጉዳዩ ላይ ጠቃሚ የጥንቃቄ ወይም የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ያመቸው ዘንድ ፍርድ ቤቱ ከማንኛውም ድርጅት ማንኛውንም ሰው ወይም እንደራሴ (የጤና፣ የማህበራዊ ሳይንስ ወይም የስነ ልቦና ባለሞያ ወይም አስተማሪዎቹን) በመጥራት ስለ አጠቃላይ ፀባዩ እና ስለ ቀድሞ ጥፋቱ መጠየቅ ይችላል። በዚህም ላይ የተከሳሹ ወገን መልስ መስጠት እና ምስክር መጥራት ይችላሉ፤ ስለቅጥቱ ሁኔታም በቃል ሊመለክቱ ይችላሉ (የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 177 እና የወ/ህ/ቁ 54)
    - ፍርዱን እንደማንኛውም መደበኛ ክስ ከሰጠ በኋላ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ውሳኔውን ያስረዳዋል፤ ለወደፊቱም ጸባዩን እንዲያርም ያስጠነቅቀዋል፤ችግሩ የተፈጠረው በወላጆቹ ወይም ሃላፊነት ባለባቸው ሰዎች ችግር መሆኑን ሲረዳ ፍርድ ቤቱ ለእነዚህ ሰዎች የማስጠንቀቂያ ምክር ሊሰጣቸው ወይም ሊወቅሳቸው ይችላል (የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 178)
    - ከጥፋተኝነት ፍርድ በኋላ ፍርድ ቤቱ በሚከተለው ሁኔታ የጥንቃቄ እርምጃዎችን እና ቅጣቶችን ይወስናል።

IV. የጥንቃቄ እርምጃወች እና ቅጣቶች

ፍርድ ቤቱ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ወይም ቅጣትን በሚወስንበት ጊዜ ዕድሜውን፣ ፀባዩን፣ የአእምሮ እና የሞራል እድገቱን እንዲሁም ቅጣቱ ወይም እርምጃው በጥፋተኛው ላይ ሊያመጣ የሚችለውን መልካም ለውጥ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት (የወ/ህ.ቁ 55)

- የጥንቃቄ እርምጃዎች

ህክምና :- ጥፋተኛው አእምሮው የደከመ፣ እድገቱ የዘገዬ እና ታመመ፣ የሚጥል በሽታ ያለበት፣ በአልኮል መጠጥ ሱሰኛነት የተጠመደ ወይም በሚያፈዙ ዕፆች ተመረዘ ሆኖ ሲያገኘው ተገቢ በሆነው የህክምና ተቋም እንዲታከም ያደርጋል። የሚቻል በሆነ ጊዜ ህክምናው ትምህርት እና ስልጠናን ያካተተ መሆን ይኖርበታል ወ/ህ/ቁ **157**

ትምህርት :- ጥፋተኛው በበጎ አስተዳደግ ያላደገ፣ በንዝህላልነት የተተወ ወይም ጠባዩ ወደ መጥፎ ስራ ያዘነበለ/የሚያዘነብል ሆኖ ካገኘው በጠባቂ ስር ሆኖ ቀጥጥር እየተደረገበት ትምህርት እና በጎ አስተዳደግ እንዲያገኝ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መስጠት አለበት የወ/ህ/ቁ **159**

- ጠባቂዎቹ እነማን ናቸው...ዘመዶቹ እነሱ ከሌሉ/ችሎታ የሌላቸው ከሆኑ ብቁ የሆነ ሰው ወይም ህፃናትን ለመጠበቅ እና ለማስተማር የተቋቋመ ድርጅት

- ምን ሃላፊነት አለባቸው… መልካም ፀባዩን የሚከታተሉ ለመሆናቸው ፍርድ ቤት ቀርበው ሃላፊነታቸውን በፅሁፍ ያረጋግጣሉ
- ማን ይቆጣጠራቸዋል… በአቅራቢያው የሚገኙ የጥበቃ ባልደረቦች ይቆጣጠራቸዋል
    - የጥበቃ ባልደረባ ፦ በመንግስት ቁጥጥር ስር ሆኖ የጥንቃቄ እርምጃዎች እና ቅጣቶች መልካም ፍሬ እንዲያገኙ የሚያደርግ አካል ሲሆን በተቻለ መጠን ይህ ተግባር ለፖሊስ ተቋማት መሰጠት የለበትም የወ/ህ/ቁ 208-210

ተግሳጽ እና ወቀሳ፦ ተገቢና መልካም ውጤት ያመጣል ብሎ ባመነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የድርጊቱን ውጤት እንዲረዳው እና ለወደፊቱም በጎ ተግባር እና መልካም ጠባይ እንዲኖረው የሚያደርግ ተግሳጽ እና ወቀሳ በጥፋተኛው ላይ ሊያከናውን ይችላል፤ ይህም ብቻውን ወይም ከሌሎች የጥንቃቄ እርምጃ ወይም ቅጣት ጋር ሊከናወን ይችላል የወ/ህ/ቁ 160

በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ተወስኖ እንዲቆይ ማድረግ ፦ ጥፋቱ ከባድ ባልሆነ ጊዜ እና በቀላሉ የሚታረም ሆኖ በታየው ጊዜ በት/ቤቱ ወይም በመኖሪያ ቤቱ ተወስኖ ሳይወጣ በትርፍ ሰዓቱ ለዕድሜው የሚስማማ ስራ በተወሰነ ስፍራ እንዲሰራ ፍርድ ቤቱ ሊያዝ ይችላል የወ/ህ/ቁ 161

ወደ ጠባይ ማረሚያ ተቋም መላክ ፦ ጠባዩን ወይንም የቀድሞ ታሪኩን መጥፎነት እንዲሁም የወንጀሉን ክብደት እና አፈጻጸም ግምት ውስጥ በማስገባት ጥፋተኛውን ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች ማረሚያ እና ማስተማሪያ ወደተቋቋመ ተቋም እንዲገባ ፍርድ ቤቱ ሊያዝ ይችላል፤ በዚህ ስፍራም ወጣቱ አጥፊ ተገቢ በሆነ ስነ ስርዓት እየተጠበቀ ትምህርቱን፣ ግብረገብነቱን እና ተገቢውን ሙያ የሚያገኝበት እና ወደ መደበኛው ማህበራዊ ኑሮ ተመልሶ በቅንነት የሚሰራበትን ሁኔታ እንዲኖር ይደረጋል የ/ወ/ህ/ቁ 162

- ወደዚህ ተቋም መላክ ውሳኔ የሚሠጠው ቢያንስ ለአንድ ዓመት ቢበዛ ደግሞ ለአምስት ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ሆኖ ለአካለ መጠን ከምደርሱበት እድሜ ሊያልፍ ግን አይችልም የ/ወ/ህ/ቁ 162 (2)

➢ የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ልዩ ሁኔታ

- ከመደበኛው የፍርድ ቤት ውሳኔ በተለዬ ሁኔታ ለወጣት ጥፋኛው ጠቃሚ ሆኖ ሲያገኘው ከላይ በተገለጸው መልኩ የተሰጡትን የጥንቃቄ እርምጃዎች ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት ራሱ ሊለውጣቸው ይችላል የወ/ህ/ቁ 164

- ከእነዚህ እርምጃዎች አንዱ የተወሰደበት ወጣት አጥፊ በወንጀል እንደተቀጣ አይቆጠርም የወ/ሕ/ቁ 165

V. ቅጣቶች

ከላይ የተዘረዘሩት የጥንቃቄ እርምጃዎች ፍሬ ሳያገኙ የቀሩ እንደሆነ/የማያስገኙ ሆነው በታየት ጊዜ የተፈጸመውን ጥፋት በማመዛዘን እና አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ የልዩ አዋቂ ምስክርነትን መሰረት በማድረግ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የቅጣት ዓይነቶች በአጥፊው ላይ ሊወስንበት ይችላል።

i) መቀጮ :- መቀጮ መክፈልን እንደ ቅጣት የሚቆጥረው እና የሚያስተምረው መስሎ ሲታየው እና ራሱ መክፈል የሚችል መሆኑን ሲረዳው ፍርድ ቤቱ አጥፊውን መቀጮ እንዲከፍል ሊፈርድበት ይችላል የወ/ህ/ቁ 167።

ልዩ ሁኔታ (የወ/ህ/ቁ **167 Vs 94** እና **95)**

- ለመቀጮው አፈጻጸም ዋስትና ወይም መያዣ እንዲያቀርቡ አይገደዱም
- መቀጮውን መክፈል ያልቻለ ወጣት አጥፊ የግዴታ ስራ እንዲሰራ አይገደድም
- መቀጮውን በተወሰነለት ጊዜ ውስጥ ካልከፈለ በምትኩ አጥፊው በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ውስጥ ተወስኖ እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል መክፈል ያልቻለ ወጣት

ii) እስራት :- ጥፋቱ አስር ዓመት /ከዚያ በላይ ጽኑ እስራት ወይም ሞት ሚያስቀጣ ከባድ ጥፋት ከሆነ አማራጭ ሁለት ዓይነት እርምጃዎች ሊወሰዱ እንደሚችሉ ተደንግጓል።

- ወደ ጠባይ ማረሚያ መላክ፡- ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የጥንቃቄ እርምጃዎች እንዲፈጸሙበት (ደህንነት ማረጋገጫ፣ ከሰው ተለይቶ የመኖር ወይም ልዩ የሆነ የስነ ስርዓት ጥበቃ እንዲደረግለት) ወደ ጠባይ ማረሚያ ተቋም እንዲላክ ማድረግ አንደኛው አማራጭ ነው።
- በቀጥታ የቅጣት መፈጸሚያ ወደሆነው እስር ቤት እንዲታሰር በማድረግ መሰረታዊ የሆነውን ከሰው ተለይቶ የማኖርን ደንብ መከተል፤ ይህ ሊደረግ የሚገባውም ጥፋተኛው አደገኛ እና ሰላምን የሚያውክ/ጸጥታን የሚያደፈርስ እና ለሌሎች መጥፎ ምሳሌ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በተረዳው ጊዜ ነው።
- የእስራት ቅጣቱ አፈጻጸም በቀላል እስራት አፈጻጸም ስርዓት ሆኖ ጊዜውም አንድ ዓመት ሳያንስ እስከ አስር ዓመት ሊደርስ ይችላል፤ ከላቂዎች ጋርም አይታሰሩም።

- ወደ ጠባይ ማረሚያ ከተላከ በኋላም በጠባዩ/ሊደርስ በሚችለው አደጋ ምክንያት ወደ እስር ቤት መላኩ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም እድሜው 18 ዓመት ሞልቶት የተወሰነበት ቅጣትም ለአካለ መጠን ከመድረሻው ጊዜ በመብለጥ የሚያሳስር ሆኖ ሲገኝ ወደ እስር ቤት ሊላክ ይችላል። ጊዜውን ለመወሰን በጠባይ ማረሚያ ተቋም የቆየበትን እና የጠባዩን የመሻሻል ሁኔታ ግንት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።
- የጠባዩ መሻሻል ታይቶ ቅጣቱን ፈጽሞ ከማጠናቀቁ በፊት በአመክሮ ሊፈታ የሚችልበት ስርዓት ተፈጸሚ ይሆናል።

2.3.2. ከአስራ አምስት ዓመት በላይ ከአስራ ስምንት ዓመት በታች ያሉ ወጣት ወንጀል ፈጻሚዎችን በተመለከተ

በዚህ እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች በወንጀል በተጠረጠሩ ጊዜ የምርመራው ሂደትም ሆነ የክስ አቀራረቡ እና የፍርድ ቤቱ የክርክር ሂደት የሚመራው መደበኛው የወንጀል ጉዳይ በሚመራበት ስርዓት ነው **(የወ/ህ/ቁ 56 እና 176)**፤ እድሜያቸው 15-18 ለሆኑት ለእነዚህ ህጻናት የወንጀል ህጋችን ጥበቃ የሚያደረገው ከጥፋተኝነት ውሣኔ በኋላ በቅጣት ጊዜ ብቻ ነው። የጥበቃው አድማስ ጠባብ ነው። ሁሉም ህጻናት ሊካተቱ ይገባል የሚል ተቃውሞ በህጻናት ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች ይደመጣል።

3.3.2.1.ልዩ ሁኔታ (የወህ/ቁ 177)

4. የይግባኝ ሥነ ሥርዓት

እንደሚታወቀው የይግባኝ መብት የሕገ መንግሥቱም ሆነ አገራችን የተቀበለችው አለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ኮቨናንት መሠረት ያለው የተፈረደበት ተከራካሪ ወገን መብት ነው። ይሄ መብት ጉዳዩ በታየበት ፍርድ ቤት በተሰጠ ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ተበድያለሁ የሚል ወገን የቅሬታ አቤቱታውን ለበላይ ፍ/ቤት በማሰማት ፍርዱ ወይም ትዕዛዙ እንዲሻርለት የሚጠይቅበት እንደመሆኑ መሠረታዊ መብት መሆኑ አያጠያይቅም። የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20/6/ ይህንኑ ያመለክታል።

የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 181 የይግባኝ አቤቱታ መርህን ያስቀምጣል የተፈረደበት ተከሳሽ ወይም ተከሳሽ ነፃ በመውጣቱ ወይም በመለቀቁ ምክንያት ይግባኝ ሊባል እንደሚችል ያሣያል። ይሁን እንጅ ይግባኝ የማይባልባቸው ጉዳዮም አሉ።

3.1. ይግባኝ የማይባልባቸው ጉዳዮች

- ጥፋተኝነቱን ያመነ ሆኖ በእምነቱ መሰረት በተሰጠ የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት የማይችል መሆኑ ተደንግጓል (የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 185 (1)) ከዚህ ጋር በተያያዘ ችግሮች የሚታዩት አንድ ተከሳሽ ጥፋቱን አምኗል የሚባለው በምን ሁኔታ ነው ለሚለው ጥያቄ በሚሰጠው ምላሽ ነው። የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134(1) ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመሥራቱ በሙሉ ያመነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል በማለት እንደሚመዘግብ ያሣያል። ከዚህ በግልጽ መረዳት የሚቻለው ለተከሳሽ ክሱን በዝርዝር እንዲያውቀው ማድረግ እንደሚገባ ነው። ሕገመንግስታችንም በአንቀጽ 20(2) ላይ ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር ለተከሳሽ እንዲነገረውና በጽሑፍም ሊያገኘው መብቱ መሆኑን ያስቀምጣል። በዚህ መልክ ክሱ ምን እንደሚል በሚገባ ሳይረዳ ተከሳሽ እምነት ክህደት ቢጠየቅና ጥፋተኛ ነኝ ቢል በሕጉ መሠረት ጥፋተኛነቱን አምኗል ለማለት በቂ ነው ማለት አይቻልም።

የችግሩን አሳሳቢነት ያጋጠሙ ሁለት ምሣሌዎችን በመጥቀስ ማሣየት ይቻላል።

ዐቃቤ ሕግ የልዩ ወ/መ/ሕ/ቁ. 214/74 አንቀጽ 17 ጠቅሶ (አሁን የተሻረ) ወንጀል በመሥራት ሃሳብ ሰነድ ደልዟል በሚል አንድን አርሶ አደር ይከሳል። ይህ አርሶ አደር በአካባቢው በመንግሥት ተወርሦ የነበረ የእህል ወፍጮ ገንዘብ ተቀባይ ነበር። የትምህርት ደረጃው ከመሠረተ ትምህርት ያላለፈ ነው። ገንዘብ እየተቀበለ ደረሰኝ ሲሰጥ ጽሑፉን ጠበቅ አድርጐ ባለመፃፉ ወይም ካርቦኑ በማርጀቱ ምክንያት ኮፒዎቹ ላይ በጽሑፍ በሚታይ መልኩ ባለመተላለፉ ይህን ለማጉላት ሲል ባደረገው ጥረት ኮፒዎቹ ይደላለዛሉ ይህ ሰው ተከስሶ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተሰጥቶት እና በአስተርጓሚ ተነግሮት እምነት ክህደት ሲጠየቅ ጥፋተኛ ነኝ ይላል። ፍ/ቤቱ ተከሳሹ ሰነዱን የደለዘው በክሱ ላይ በዝርዝር በተቀመጠው ሁኔታ ወንጀል በመሥራት ሃሳብ ለመሆኑ አልጠየቀውም ተከሳሹ ከክሱ የተረዳው ሰነድ ደልዘሃል መባሉን ብቻ ነበር። ነገር ግን ጥፋቱን አምኗል ተብሎ 10 ዓመት ጽኑ እሥራት ተፈረደበት።

በ 1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ወቅት በየቦታው የወዳደቁ መሣሪያዎች በአንዱንድ አርሶ አደሮች እጅ ገብተው ነበር። አንዳንዶቹም ከቀድሞ መንግሥት ወታደሮች በትንሽ ገንዘብ ገዝተው ከሌባና ከአውሬ መከላከያ ይሆነናል በሚል አስቀምጠው ሣለ ለሕግ ወጥ ዓላማ መሣሪያዎቹን ይዘው ተገኝተዋል በሚል ክስ ተመሥርቶባቸው ፍ/ቤት ሲቀርቡ ጥፋተኞች ነን ይላሉ። ፍ/ቤቶች ተከሳሾቹ

ሙሉ በሙሉ በክሱ ዝርዝር የጠቀሱትን ነገሮች ለመፈፀማቸው ጠይቀው ሳያረጋግጡ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል በሚል ብቻ ለሕገወጥ ዓላማ መሣሪያ ይዞ መገኘቱ የተረጋገጠበት አጥፊ በሚቀጣበት ቢያንስ የ 5 ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት በሚያስቀጣ አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት ተወስኖባቸዋል። እነዚህ ተከሳሾች በአግባቡ ተጠይቀው ቢሆን መሣሪያዎቹን የያዙት ራሳቸውን ከአውሬና ሌባ ለመከላከል እንጂ ለሕገወጥ አላማ አለመሆኑን ባስረዱ ነበር።

አንድ ተከሳሽ ጥፋተኛ ነኝ ሲል ፍ/ቤት ጥፋተኛ ነኝ ያለበትን ምክንያት በዝርዝር ሊጠይቀው እና የክሱን ዝርዝር በሙሉ ማመኑን (ወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.134) ማረጋገጥ ይኖርበታል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ ተከሳሽ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134 መሠረት ክሱን በሙሉ እንዳመነ ተቆጥሮ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 185 እንደተመለከተው በጥፋተኝነት ውሣኔው ላይ ይግባኝ ለማለት ሊከለከል አይገባም።

- በሌለበት የተሰጠ ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በሚል በተሰጠ ውሳኔ ላይ (202 (3)) (የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 161) ፤ ይግባኝ የተከለከለው ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ብቻ ነው ወይንስ አጠቃላይ በጥፋተኝነት ውሳኔው ላይ?) በጥፋተኝነቱም ጭምር ነው የሚባል ቢሆን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ሳያልፍ ተከሳሹ ቀርቦ ይግባኝ በጥፋተኝነቱ ላይ ይግባኝ ቢያቀርብ ይችላል ወይ? በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 193 መሰረት የይግባኝ ክርክሩ በሌለበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ላይ የሚቀርበው የይግባኝ ስርዓት የሚከተለው መደበኛውን የይግባኝ ስርዓት ነው? ወይስ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 202 (3)? (የሰበር መዝገብ ቁጥር 57632 - ቅጽ 12 ገጽ 179)
- ጊዜዓዊ በሆኑ ትዕዛዛት ላይ (184)
    - ቀጠሮ መስጠትን ወይም አለመስጠትን አስመልክቶ (94)
    - የቀረበን መቃወሚያ አስመልክቶ (131) እና
    - ማስረጃ መቀበልን ወይም አለመቀበልን አስመልክቶ በሚሰጡ ትዕዛዞች (146) ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ አሁን ያለው አሰራር የሚያሳየው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ እያከራከረ ያለው ፍርድ ቤት ተከሳሹ ተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት መፈጸሙ ተረጋግጦበታል በሚል እንዲከላከል በሚሰጠው ትዕዛዝ ከፍርድ በፊት ይግባኝ

የማይባልበት መሆኑን ነው። በሌላ በኩል በስር ፍርድ ቤቱ ሊከላከል አይገባውም ተብሎ የተሰጠውን ፍርድ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመሻር ሊከላከል ይገባል በሚል ወደስር ፍርድ ቤት በመመለስ በሚሰጠው ፍርድ ላይ ይግባኝ ሊባልበት ይችላል ወይ?

- የጊዜ ቀጠሮን በመፍቀድ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት ይቻላል ወይ (የመ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 185 የህገ-መንግስቱ አንቀጽ 20 (6))

3.2. የይግባኝ ስልጣን እና ደረጃ

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መጽሐፍ በ1954 ዓ.ም የወጣ እንደመሆኑ ይግባኝ አቀራረብን በተመለከተ ከቁ 182-183 የተቀመጡት የድሮውን የፍርድ ቤቶች መዋቅርና አደረጃጀት የሚያሣዩ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ያለውን የፌዴራል ሥርዓት ተከትሎ ፍ/ቤቶችም በፌዴራልና በክልሎች ተደራጅተዋል። በዚሁ መሠረት በፌዴራል ደረጃ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሲኖሩ በክልሎችም ወረዳ ፍ/ቤት፣ ዞን፣ (ከፍተኛ) ፍ/ቤትና ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች አሉ።

በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሠረት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይቀርባል። ውሣኔው በይግባኝ ከፀና ሁለተኛ ጊዜ ይግባኝ ማለት አይቻልም። ነገር ግን በውሣኔዎቹ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል አቤቱታ ሲኖር ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ማመልከት እንደሚቻል ተደንግጓል በተመሳሳይ ሁኔታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ታይቶ በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ነው። (አንቀጽ 9 እና 13)። የክልላችን ፍርድ ቤቶችን በተመለከተ ደግሞ ተሻሽሎ በወጣው በዝክረ ህግ አዋጅ ቁጥር እንደተገለው በወረዳ ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን እንደሚያቀርብ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የስር ፍርዱን ካጸናው ይግባኙን ላቀረበው ተከራካሪ የመጨረሻ ውሳኔ እንደሚሆን ተደንግጓል። እንዲሁም የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ይግባኝ ሊያቀርብ እንደሚችል እና በተጨማሪም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በይግባኝ አይቶ የስር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመሻር/በማሻሻል የተለዬ ውሰኔ በሰጠ ጊዜ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ መልስ ሰጭ ሆኖ ሲከራከር የነበረው ተከራካሪ ቅር ከተሰኘ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ የሚችል መሆኑን ህጉ ያስረዳል። በዚህ መልኩ በየደረጃው ያሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ

የህግ ስህተት ተፈጽሞብኛል በሚል ቅር የተሰኘ ተከራካሪ የሚያቀርበውን ቅሬታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ማሰማት ይችላል።

ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ በተግባር እየታዬ ያለው ችግር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የይግባኝ ክርክሩን ተመልክተው የስር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በከፊል በማሻሻል (በከፊል በመሻር በከፊል በማጽናት) ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ሁለተኛ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለው ጉዳይ ነው? ለምሳሌ የጥፋተኝነቱን ውሳኔ በማጽናት ቅጣቱን ግን በማሻሻል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ባዩ ጭራሽ ጥፋተኛ ልባል አይገባኝም ነበር በሚል ወይም ቅጣቱ የበለጠ ሊሻሻልልኝ ይገባ ነበር በሚል ለቀጣዩ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል ወይ? የሚለው ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ ተወያይቶ ከህጉ አንጻር ተገቢውን ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል።

3.2. ይግባኝ የሚቀርብበት ጊዜ

በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 187 ላይ እንደተመለከተው ይግባኝ የሚጠየቀው ፍርድ በተሠጠ በ 15 ቀናት ውስጥ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የሚፈረድባቸው ተከሳሾች ማረሚያ ቤት ስለሚገቡ በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ ያለመጠየቃቸውን ማረጋገጥ የሚያስቸግርበትና ጊዜው አልፏል እየተባለ የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻ ለማቅረብ የሚገደዱበት ሁኔታ አለ። ችግሩ በዋናነት በሁለት ምክንያቶች ሊከሰት ይቻላል።

1. ተቀጪው እንደተፈረደበት ይግባኝ ማለቱን ለማስታወቅ በ 15 ቀን ውስጥ ማመልከቻውን ጽፎ ሊሆን ይችላል። እስረኛ በመሆኑ ራሱ ፍርድ ቤት ሊወስደው ስለማይችል የሚሰጠው ለማረሚያ ቤቱ ነው። ማረሚያ ቤቱ በተለያዩ ምክንያቶች በ 15 ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ለፍ/ቤት ሣያስተላለፍ የሚቆይበት አጋጣሚዎች አሉ።

2. የይግባኝ መጠየቂያ ማመልከቻው ፍርዱ በተሰጠ 15 ቀን ውስጥም የተፃፈ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ነገር ግን ለፍ/ቤት ከረጂም ጊዜ በኃላ ይላክና ማረሚያ ቤቱ ማረጋገጫ እንዲሠጥ ሲጠየቅ ታራሚው መቼ ማመልከቻውን እንደሰጠው ማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ ይከሰታል።

የመጀመሪያውን በተመለከተ ጥፋቱ የታራሚው ባለመሆኑ ይግባኙን ለመቀበል ብዙ ላያስቸግር ይችላል። በሁለተኛው ሁኔታ ግን ታራሚው ይግባኝ መጠየቂያ ማመልከቻውን ፍርድ በተሰጠ በ 15 ቀን ውስጥ እንደፃፈ በማድረግ ጊዜው ካለፈ በኋላ ለማረሚያ ቤቱ ሊያቀርብ የሚችልበት ሁኔታ ስለሚኖር ፍ/ቤቱ ተጨማሪ ማጣራቶችን ማድረግ ሊያስፈልገው ይችላል።

ይግባኙ በጊዜው መጠየቁ ከተረጋገጠ ሌላው ሊታይ የሚገባው ፍርዱን የሠጠው ፍርድ ቤት የፍርዱን ግልባጭ ለታራሚው በማረሚያ ቤት በኩል የሚያደርስበት ጊዜ ነው። ታራሚው (ይግባኝ ባይ) የፍርድ ግልባጭ በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርድ ለሠጠው ፍ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል (ቁ. 189)።

በዚህ ረገድም ችግሮች ይታያሉ ታራሚው የፍርድ ግልባጭ የሚደርሰው በማረሚያ ቤት በኩል እንደመሆኑ መጠን ፍርድ ግልባጩ ደረሰው የሚባለው የመዝገብ ሹሙ (ሬጅስትራሩ) ግልባጩን ለማረሚያ ቤቱ የላከበት ቀን ነው ወይንስ ማረሚያ ቤቱ ለአመልካቹ አስፈርሞ የሚሠጥበት ቀን ነው የሚለው በተግባር ቀላል ሆኖ አይታይም። ሕጉ የፍርድ ግልባጭ ለማረሚያ ቤቱ የደረሰበትን ቀን እንደ መነሻ የወሰደ ይመስላል፡ (ቁ 187(1))ይህም ያለ ምክንያት አይደለም። ታራሚው የሚገኝበት ማረማያ ቤት ፍርድ ግልባጩ እንደደረሰው በእለቱ ለአመልካች ይሠጣል በሚል እሳቤ ነው። አንዳንዴ ግን እውነታው ከዚህ የተለየ ነው። በተለያዩ ምክንያቶች የፍርድ ግልባጭ ለማረሚያ ቤቱ ጽ/ቤት ደርሦም በእለቱ ለታራሚው ሳይሰጥ ሊቆይ ይችላል በዚህ የተነሳም ታራሚው የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርድ በደረሰው 30 ቀናት ውስጥ (ለማረሚያ ቤት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ እየተቆጠረ ማለት ነው) አላቀረበም የሚባልበት ሁኔታ ካለ ለመዘግየቱ ተጠያቂው ማን መሆኑ ሊጣራ የሚገባው ከመሆኑም በላይ የፍርድ ግልባጭ ለታራሚው ደረሰ ሊባል የሚገባው ለራሱ የደረሰበት እንጂ ለማረሚያ ቤቱ የተላከበት ቀን ሊሆን አይገባውም የሚል እምነት ያላቸው ዳኞች አሉ።

ከዚህም በተጨማሪ የፍርድ ግልባጭ ለማረሚያ ቤት በደረሰበት ቀን ለታራሚውም ደርሦ ታራሚው የይግባኝ ማመልከቻውን ሠላሣ ቀን ከመሙላቱ በፊት ጽፎ ለማረሚያ ቤቱ ቢያስረክበም ለፍ/ቤት ዘግይቶ የሚደርስበት አጋጣሚም አለ። እነዚህን ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ ሁለት ዓይነት አቋሞች የታያሉ።

I. የመጀመሪያው አተረጓጎም፡- በታራሚው በኩል ለመዘግየቱ አስተዋጽኦ እስከሌለ ድረስ ይግባኙ ሊታይ የሚገባው ነው። ስለሆነም የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈው በማረሚያ ቤቱ ምክንያት

መሆኑን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ካረጋገጡ የይግባኝ ማስፈቀጃ እንዲቀርብ ማድረግ ብዙም ትርጉም ያለው ባለመሆኑ የይግባኝ ማስፈቀጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ የይግባኝ ቅሬታው ቀርቦ ሊታይ ይገባል የሚል ነው።

II. ሁለተኛው አተረጓጎም፡- በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ መልኩ የዘገዩበት ምክንያትም ቢሆን እንደሌሎቹ ምክንያቶች ሁሉ በይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ቀርቦ እና ታይቶ ሊወሰን ይገባዋል የሚለው ነው። የህጉን ዝርዝር ሁኔታ ስንመለከተው ግን ሁለተኛውን ትርጉም የሚደግፍ ይመስላል።

በሌላ በኩልም ይግባኙን የሚያዬው ፍርድ ቤት ተከሳሹ ከታሰረበት ማረሚያ ቤት ርቆ በሚገኝበት ሰዓት ታራሚው ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊሰማ የማይችልበት አጋጣሚ በሚኖርበት ጊዜ የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ/ዉሳኔ በጊዜው ባለመገለጹ ምክንያት የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ሊያልፍ የሚችልበት አጋጣሚም በአሰራር በብዛት የሚታይ በመሆኑ ዳኞች ታራሚዎች መቅረብ ባልቻሉበት ሁኔታ የሰጠው ትእዛዝ/ውሳኔ ታርሚዎቹ እንዲያዉቁት ማድረግ እና ትዕዛዙ ወጭ ሆኖ የመላኩን ሁኔታ በሚገባ ሁኔታ ማረጋገጥ ይኖርበታል።

II.3. የየግባኝ ክርክር ስለሚሰማበት ሁኔታ

የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 192 የይግባኝ ክርክር ስለሚሠማበት ሁኔታ የሚደነግግ ነው የይግባኝ ክርክር በችሎት የሚሠማ እንደመሆኑ በቃል የሚደረግ ነው። የግራ ቀኙም ክርክር በአንድ ቀጠሮ የሚጠናቀቅ ነው ይህን ሕግ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ በሕግ ባለሙያ በማይታገዙ ግለሰቦች በኩል ችግር አለ። በቃል ክርክራችንን ማሰማት አንችልም እያሉ በጽሑፍ መልሳቸውን ያቀርባሉ በግድ በቃል ክርክራችሁን አሰሙ ማለት መብታቸውን ማጣበብ ይሆናል በሚል መልሳቸውን በጽሑፍ መቀበል የማይታለፍ ይሆናል የሌላውን ወገን የመ/መልስ መስማት አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ ቀጠሮ ለመለወጥ ምክንያት ይሆናል።

ከፍ ሲል እንደተገለፀው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 161 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ተለይተው ከተገለፁ ወንጀሎች ውጭ አንድ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት አይታይም በይግባኝ ደረጃ ግን ወንጀሉ ምንም ቢሆን መ/ሰጭ ካልቀረበ ይግባኙ በሌለበት መስማቱ ይቀጥላል (ቁ.193)። የዚህን እንድምታ ወይም አመክንዮ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በዋናነት የሚመረምረው በሥር ፍ/ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎች ነው የሚል እምነት ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ማስረጃ መስማት/መቀበል አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ምክንያቱን ጽፎ ማስረጃውን መቀበል እንደሚችል የፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 194 ያሣያል። ተከራካሪ ወገኖች ይህንን ለፍ/ቤቱ የተሠጠን ሥልጣን ለመጠቀም በመፈለግ በሥር ፍ/ቤት ሊያቀርቡ ሲችሉ ያለፉት ማስረጃ እንዲቀርብላቸው የሚጠይቁበት ጊዜ ስላለ ፍ/ቤቱ

ማስረጃውን ከመቀበሉ በፊት የማስረጃውን ወሳኝ መሆን በጥንቃቄ ማገናዘብ ይገባዋል። በዚህ ረገድ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የሚቀበለው ተጨማሪ ማስረጃ በስር ፍርድ ቤቱ እንደቀረበ ማስረጃ ይቆጠራል።

የይግባኝ ክርክር ከተጠናቀቀ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረዝ የጥፋተኝነት ውሣኔ በማጽናት ቅጣት መቀነስ ወይም በሥር ፍ/ቤት በነፃ የተለቀቀን ተከሳሽ ጥፋተኛ በማድረግ መቅጣት ይቻላል። ወይንም ደግሞ ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ እንደገና እንዲታይ ማዘዝ የሚችል መሆኑ በህግ ተደንግጓል (ቁ. 195)።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ቅጣት በዛበኝ ብሎ ይግባኝ ባቀረበ ተከሳሽ መዝገብ ላይ ዓ/ህግ ቅጣቱ ያነሰ ስለሆነ ክፍ ብሎ ሊቀጣ ይገባል የሚል መከራከሪያ በሚያቀርብበት ጊዜ በእርግጥም ቅጣቱ ያነሰ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ቢገነዘብ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን አክብዶ መወሰን ይችላል ወይ? የሚለውን ስንመለከተው አይችልም፤ ምክንያቱም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅጣት መቀነስ ወይም መጨመር የሚችል ቢሆንም ቅጣት በዛበኝ ብሎ ይግባኝ በጠየቀ ይግባኝ ባይ ላይ ቅጣት መጨመር ባልተጠየቀ ዳኝነት መፍረድ ስለሚሆን እና ዓ/ህግም ቅጣት አንሷል የሚል ከሆነ በራሱ ህግን በመከተል ይግባኙን ማቅረብ እንጅ በተከሳሹ ይግባኝ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችልበት ህጋዊ አሰራር ባለመኖሩ ነው።

በይግባኝ ውሳኔ ከመስጠት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላኛው አከራካሪ ነጥብ ዓ/ህግ ይግባኝ ባዩ በነጻ ሊሰናበት/ቅጣቱ ሊቀልለት ይገባል የሚል መልስ ባቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የስር መዝገቡን ሁኔታ ሳይመለከት ይግባኝ ባዩን ዓ/ህጉ ባሳሰበው መሰረት በነጻ ማሰናበት ወይም ቅጣቱን ማሻሻል ይኖርበታል ወይ?

II.4. የተፈረደባቸው ሰዎች ብዙ ሆነው አንዱ ብቻ ይግባኝ ሲያቀርብ (196)

- በይግባኝ የተሰጠው ፍርድ ለይግባኝ ባዩ የሚጠቅመው በሆነ ጊዜ እና
- ተከሳሾቹ ይግባኝ ቢሉ ኖሮ በፍርዱ እነርሱም ይጠቀሙ የነበረ በሆነ ጊዜ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ላላሉትም ይግባኝ እንዳሉ ተቆጥሮ ይፈጸምላቸዋል።

ይህንን ባለመገንዘብ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሳይሰጥ ቢቀር ይግባኝ ባላላንበት ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ስለሚጠቅመን ለእኛም ተፈጻሚ ሊሆንልን ይገባል የሚሉ ተከሳሾች አቤቱታ ለማን እና እንዴት ሊታይ ይገባል።

II.5. በነጻ በተለቀቀ ተከሳሽ ላይ ዓቃቤ ህግ ይግባኝ ባለ ጊዜ የዋስትና ጥያቄ የሚስተናገድበት ሁኔታ

እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በተከሰተ ጊዜ በተለያዩ ዳኞች ሶስት ዓይነት ትርጉሞች እየተሰጡ ሲተገበሩ ይታያል።

- የጉዳዩ አይነት ምንም ይሁን ምን የዋስትና ጉዳይ በጭብጥነት አይነሳም (የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 193፣ በህገ-መንግስቱ ጥፋተኝነት በፍርድ እስክረጋገጥ ድረስ እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት 20 (3)).
- የዋስትና ጉዳይ በጭብጥነት መያዝ አለበት፤ የተጠረተሩበት እና ዓ/ህግ ይግባኝ ያለበት ወይንም የሰበር አቤቱታ ያቀረበበት ጉዳይ ተከሳሹን ያስቀርባል ተብሎ ክርክር የሚደረግበት በሆነ ጊዜ እና ጉዳዩም ከመነሻው ዋስትና የሚያስከለክል በሆነበት ጊዜ ተከሳሹ ተይዞ ጉዳዩን በማረሚያ ቤት ሆኖ እንዲከታተል ሊደረግ ይገባል (የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 63፣ ከ 10 ዓመት በላይ ሊያስቀጡ በሚችሉ የሙስና ጉዳዮች)። ዋስትና በማይከለክሉ ጉዳዮች ላይ ከወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 67 አንፃር እየታየ የዋስትናው ጉዳይ እልባት እንዲያገኝ መደረግ አለበት።
- የዋስትና ጉዳይ በጭብጥነት መያዝ አለበት፤ የጉዳዩ አይነት ምንም ይሁን ምን የዋስትና ጉዳዩ ከወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 67 አንፃር እየታየ የዋስትናው ጉዳይ እልባት እንዲያገኝ መደረግ አለበት።

II.6. ፍርድ እንዳይፈጸም ስለሚታገድበት ሁኔታ (የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 188)

የማይታገዱ የፍርድ ዓይነቶች

- ለጥንቃቄ ሲል እንዲፈጸሙ በሚል የተሰጡ ትዕዛዞች
- ካሳ ወይንም ኪሳራ ይክፈሉ በሚል የተሰጠ ፍርድ

በጥፋተኝነት ፍርድ ላይ ያስቀርባል ተብሎ የይግባኝ /የሰበር/ ክርክር በሚካሄድበት ጊዜ ፍርዱ ሳይፈጸም ታግዶ ሊቆይ የሚችለው ለሁሉም ዓይነት ጉዳዮች ነው ወይ?